ከአዋቂዎች ጥበቃ አገልግሎቶች ጋር

# የራሳችንን ድርሻ ከመወጣት

Adult Protective Services
Virginia Department for Aging and Rehabilitative Services

## የአዋቂዎች ጥበቃ አገልግሎት (APS) ምንድን ነው?

ኤፒኤስ (APS) በእድሜ ከፍ ያሉ አዋቂዎች እና የአካል ጉዳተኞች ላይ ደረሱ የተባሉ መጠቃትን/ረገጣን፣ ችላ መባልን፣ ራስን ችላ ማለትን እና ብዝበዛን በመመርመር በክብር እና በአክብሮት እንዲኖሩ በመርዳት ላይ ያተኮረ የማህበራዊ አገልግሎቶች ፕሮግራም ነው።

## የኤፒኤስን አገልግሎቶች ማን መቀበል ይችላል?

በቨርጂኒያ ውስጥ ኤፒኤስ የሚከተሉትን አዋቂዎች ያገለግላል፦

- ✓ ዕድሜያቸው 60 እና ከዚያ በላይ የሆኑትን፣ ወይም
- ✓ ዕድሜያቸው ከ18-59 እና አቅመ ደካማ የሆኑትን
- ✓ በመንግሥት ማረሚያ ቤቶች ካልሆነ በስተቀር በማህበረሰብ ውስጥ ወይም በመኖሪያ ቤት ውስጥ የሚኖሩ

## እርስዎ መጠቃትን/መበደልን፣ ችላ መባልን፣ ራስን ችላ ማለትን፣ እና ብዝበዛን እንዴት ይገልጹዋቸዋል?

ከዚህ በታች አንዳንድ የተለመዱ ትርጓሜዎች አሉ። ለበለጠ መረጃ ድህረ ገጻችንን ይጎብኙ dars.virginia.gov/aps/

**ጥቃት/መበደል (Abuse)**

ጥቃት/መበደል የአካላዊ፣ አዕምሯዊ ወይም ጾታዊ ጥቃትን ያጠቃልላል።

ራስን ችላ ማለት አንድ አዋቂ ሰው ጎልማሳ የራሱን አስፈላጊ አካላዊ፣

**ችላ መባል (Neglect)**

ችላ መባል የሚከሰተው እንክብካቤ ሰጪው ለጎልማሳው እንደ ምግብ፣ ልብስ፣ መጠለያ ወይም አስፈላጊ የህክምና እንክብካቤን የመሳሰሉ በቂ ድጋፍ መስጠት ሳይችል ሲቀር ነው።

**ራስን ችላ ማለት (Self-Neglect)**

ሥነ-ልቦናዊ፣ ወይም ማህበራዊ ፍላጎቶች ማሟላት በማይችልበት ጊዜ ነው፣ ይህም የጎልማሳውን ጤንነት፣ ደኅንነት እና በደኅና ሁኔታ መሆንን አደጋ ላይ ይጥላል።

**ብዝብዛ (Exploitation)**

ብዝበዛ ማለት አንድ ሰው ጎልማሳውን ወይም ገንዘቡን ለግል ጥቅም ወይም ለገንዘብ ማግኛ ሲጠቀምበት ነው።

## እርስዎ ሪፖርት የሚያቀርቡት እንዴት ነው?

1. በሰነዱ መጨረሻ ላይ ያለውን መረጃ በመጠቀም ኤፒኤስን ያነጋግሩ።
2. የሚከተሉትን መረጃዎች ማቅረብዎን ያረጋግጡ፣ ነገር ግን እርስዎ ከፈልጉ ማንነትዎን ሳያሳውቁ ይህን ሪፖርት ማድረግ እንደሚችሉ አባክዎ ልብ ይበሉ፦
   - ✓ የጎልማሳው ስም፣ ዕድሜ/የትውልድ ቀን፣ ወይም ሌላ የሚለይ መረጃ
   - ✓ ግለሰቡ ለጥቃት/ለመበደል፣ ራስን ችላ ለማለት፣ ለችላ መባል ወይም ለብዝበዛ የተጋለጠበት ምክንያት።
   - ✓ የሁኔታው መግለጫዎች፣ ጥቃት/በደል አድርሷል የተባለውን ማንነት የሚጠቁሙ አስፈላጊ መለያዎች ወይም በመኖርያ አከባቢ ውስጥ ያሉ ሌሎች አደጋዎች።






## ለምን ሪፖርት ማድረግ ይኖርብዎታል?



አብዛኛዎቹ በእድሜ ከፍ ያሉ አዋቂዎች እና የአካል ጉዳተኞች ያለእርዳታ ራሳቸውን ችለው ይኖራሉ። ይሁን እንጂ፣ አንዳንዶች በሌሎች ጥቃት/መበደል፣ ችላ መባል ወይም ብዝበዛ የሚደርስባቸው ሲሆን የሰለጠኑ ባለሙያዎች ለጥቃታቸው እንዲሚገቱ ያስፈልጓቸዋል። ሌሎች ደግሞ የዕለት ተዕለት ተግባራቸውን ለማከናወን እየታገሉ እና ጤንነታቸውን እና ኢጥገኝነታቸውን (ራስን መቻላቸውን) ለመጠበቅ በቤት ውስጥ ድጋፍ ከሚሰጡ አገልግሎቶች ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ።

ኤፒኤስ የእያንዳንዱን ግለሰብ ልዩ ፍላጐቶች በመገምገም ያግዛል፣ ከዚያም የአዋቂውን (የጎልማሳውን) ደኅንነት፣ ጤና እና ኢጥገኝነት (ራስን መቻል) ለመደገፍ የአገልግሎት እቅድ ያዘጋጃል።



## ሪፖርት ካደረጉ በኋላ ምን ይሆናል?

ኤፒኤስ የሪፖርቱን ትክክለኛነት ይገመግማል እና የተጠረጠረውን ጥቃት/መበደል፣ ችላ መባል፣ ራስን ችላ ማለትን ወይም ብዝበዛን ይመረምራል እንዲሁም ግለሰቡ አገልግሎቶቹን ለመቀበል ከፈለገ ግለሰቡን ከድጋፍ አገልግሎቶች ጋር ያገናኛል።



እያንዳንዱ አዋቂ የራሱን እድል በራሱ የመወሰን መብት እንዳለው እንገነዘባለን፣ ኤፒኤስ (ከተወሰኑ ሁኔታዎች በስተቀር) ማንንም ሰው እርዳታ እንዲቀበል ማስገደድ አይችልም፣ ያ ሰው እርዳታውን ሊቀበለው የማይፈልግ ከሆነ። ኤፒኤስ ተቋማትን ወይም አቅራቢዎችን የመቅጣት ሥልጣን የለውም። የሕግ አስከባሪ አካላት የወንጀል ምርመራ ይከፍቱ እንደሆነም መቆጣጠር አንችልም። የኤፒኤስ ምርመራዎች ሚስጥራዊ ናቸው ስለዚህ የምርመራውን ዝርዝር ልንሰጥዎ አንችልም።

## እርግጠኛ ካልሆኑስ?

እርስዎ ስለ አንድ ሁኔታ የሆነ “ስሜት” ያለዎ ቢሆንም ዝርዝር ጉዳዮቹን ማረጋገጥ የማይችሉ ነዎት? የኤፒኤስ ባለሙያዎች እንደዚህ ያሉትን ሁኔታዎች ለማስተናገድ የሰለጠኑ ናቸው። በእርስዎ ሪፖርት ላይ በመመስረት፣ ኤፒኤስ ሁኔታውን ይገመግማል እና እንዴት በጥሩ ሁኔታ ምላሽ መስጠት እንደሚቻል ይወስናል። የአካባቢዎ መምሪያ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ የተሻለውን የድርጊት አካሄድ ሊወስን ይችላል።



Adult Protective Services

Virginia Department for Aging and Rehabilitative Services

የተጠረጠሩትን የአዋቂዎች ጥቃት/መበደል፣ ቸል መባል ወይም ብዝበዛ ሪፖርት ለማድረግ፣ የእርስዎን አካባቢያዊ የማህበራዊ አገልግሎት ክፍል ወይም የ የ24-ሰዓት፣ ከክፍያ ነጻ በሆነው በዚህ የኤፒኤስ የስልክ መስመር ይደውሉ፦ (888) 832-3858.